# ያገራችን በዓል

እነ ስም አይጠሬ ፣ እነ ጉግ ማንጉጉ
ያልባንያ ካድሬ ፣ ያረብ ተላላኪ ፣ የእውቀት መፃጉ
የማያውቅቁበትን ፣ ወግና ማዕረጉ
እንዴት በኢትዮጵያ ፣ እንዲህ ይውረግረጉ
ችግሩ ከኛ እንጂ ፣ እነሱስ ምን ያርጉ
መቅጨት ድሮ ነበር ፣ እንደዚህ ሳያድጉ ።

በሹምባሽ ባንዳዎች ፣ ዘመን ተለውጦ
አገር እንዳወጣች ፣ ለባዕዳን ሸጦ
ያገሩን ሃብት ዘርፎ ፣ ኪሱን አሳብጦ
ሕዝብና ባህሉን ፣ እንዳሻው እረግጦ
ዲሞክራሲ ይለናል ፣ አይኖቹን አፍጥጦ
የሚነቅለው ቢያጣ ፣ ቢጠፋ ወረንጦ
ሰው ይበላ ጀመር ፣ ጥርሶቹን አግጥጦ ።

ዘንድሮ በዓላችን ፣ እንዴት ተከበረ?
ደመራ ፣ ኢሬቻ ፣ አሸንዳን ጨምሮ እንደምን ነበረ?

የጎንደር ፣ የጎጃም ፣ የሸዋ ፣ የወሎ፣ የተባለ አማራ
ኢትዮጵያ እና አንድነት ፣ እያለ የሚጣራ
እንዴት አከበራት ፣ ዘንድሮን ደመራ?

ችቦውን አቃጥሎ ፣ ልክ እንዳባቶቹ
ሃይ ሎጋው እያሉ ፣ ወጣት ጎረምሶቹ
በእልልታ ታጅቦ ፣ በናት ባባቶቹ
አክብሮት ዋለ ወይ ፣ ልክ እንደ ጥንቶቹ
ወይስ ከል ለበሰ ፣ ባዘን ተቆራምቶ
ልጆቹን ባጋዚ ፣ ጥይት አስበልቶ ።

እንዴት አከበረው ፣ አማራው ወገኔ?
ልጁን የገበረው ፣ ለትግሬው ወያኔ ።

ከቤቱ ዋለ ወይ ፣ ሃዘን አጥልቶበት
ቅል ባለቀን ሆኖ ፣ ድንጋዩን ሰብሮበት
መከራና ስቃይ ፣ እንደጉድ ዘንቦበት
ያጋጣሚ ነገር ፣ ቀን ዘንበል ብሎበት
ቀረ ወይ ሳይወጣ ፣ ሃዘን ስላለበት
በወያኔው እበት ፣ ቀን ተበላሽቶበት ።

ኦሮሞስ ወገኔ ፣ በዓል እንዴት ዋለ?
ተከብሮ ዋለ ወይ ፣ ካምናው በተሻለ ።

እንዳትተነፍስ ፣ በጭስ እያፈኑህ
ያሁኑ ይባስ ብለው ፣ ጭራሽ ገደል ገፉህ ።

አዘንኩኝ ወገኔ ፣ የዘንድሮ ኢሬቻ
ዓመት ባሉ  ቀርቶ ፣ ሆኖ መተረቻ
ቀድሞ በታቀደ ፣ ባጋዚ ዘመቻ
ቀኗን አሳለፍካት ፣ በማልቀስ በዛቻ
ደስታው ቀረና ፣ ሙታን መቁጠር ብቻ ።

ግን ዛሬ ግልጽ ሆኖ ፣ በደንብ ይታየኛል
መቃብር ተከፍቶ ፣ ወያኔን ይቃኛል
የኢሬቻው እልቂት ፣ ማብቂያው ይመስለኛል ።

ወያኔ ጉድጓዱን ፣ ቢሸፍቶ ቆፈረ
ከምን ጊዜም በላይ ፣ ሕዝቡን አማረረ
ምነው እናቱ ሆድ ፣ ሽል ሆኖ በቀረ
ካይሞቱ አሟሟት ፣ ይሻለው ነበረ
ግን ውሻ ነውና ፣ የውሻ ሞት ፣ ይሙት እየተመተረ  ።

ደግሞስ ወደሰሜን ፣ እንዴት ነው አሸንዳ
እንዴት ተከበረ ፣ በዚያ ምድረበዳ
በዓል ሸጋ ነበር ፣ ከናጅሬ ዘንዳ
ከሃረር ከባሌ ፣ ሰንጋ እየተነዳ
ነጭ ጤፍ ተጋግሮ ፣ የመጣ ከአዳአ
በጎጃም ማር ጠምቀው ፣ ጠጁ እየተቀዳ
ውስኪ እየተራጨ ፣ ሲበላ ፍሪዳ
አማራና ኦሮሞ ፣ በሚከፍሉት እዳ
በወርቅ ተስቆጥቁጣ ፣ የትግራይ ኮረዳ
ምርጡ ዘር ጨፈረ ፣ ተጠጣ ተቀዳ
ተሳክረው አለፈ ፣ የዘንድሮ አሸንዳ ።

እንግዲህ ወገኔ ፣ ይህን እያያችሁ
ይሄኛውም ያኛው ፣ አንድ ነው ካላችሁ
ፍትህ እኩልነት ፣ አመጣን ሲሏችሁ
ጭንጋፍ ወያኔዎች ፣ ሲያላግጡባችሁ
እንደ እፍኝ ቆሎ ፣ የማይሞሉ እጃችሁ
እስከመቼ አቃጥለው ፣ ለብልበው ይፍጇችሁ
ለዚህ መፍት ሄውን ፣ መቼም አልነግራችሁ
ለብልህ አይመክሩም ፣ ያውቀዋል ልባችሁ ።

ታዛቢው